





## በኢትዮጵያ ለኮቪድ 19 ወረርሽኝ መከላከያ የሚውሉ 74,800 የፊት ማስኮች እርዳታ ተለገሰ::

የኮሮና ቫይረስ በሀገራችን ተስፋፍቶ ጉዳት እንዳያስከትል መንግስት አስፈላጊውን የመከላከል ስራ እያከናወነ መሆኑ ይታወቃል። ለዚህም በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ይህ ቫይረስ በሀገራችን ላይ የሚያደርሰውን አስከፊ ጉዳት ለመቀነስ በሚደረገው ርብርብ የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ ተላልፏል:: በዚህም መሠረት በቤልጂየም ነዋሪ የሆኑ ትውልደ ኢትዮጵያዊ አቶ ዮሀንስ ዘርፉ በራስ ተነሳሽነት በ “የኔታ ቤት” ስም አስተባባሪነት ከPorton Pharma Solution Ltd. ከተባለ ድርጅት ለኢትዮጵያ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከላከያ አገልግሎት ላይ የሚውሉ በቁጥር 74,800 KN95 የጤና ባለሙያዎች የፊት ማስኮች በገንዘብ 187,000.00 ዶላር (ብር 6.495 ሚሊዮን) የሚያወጣ ለሀገራችን በእርዳታ ተለግሰዋል::

በአሁኑ ሠዓት በአገራችን ያለው የኮረና ወረርሽኝ ለመከላከል በሚደረገው ርብርብ ዙሪያ በውጭ ያለው የዳያስፖራ ማህበረሰብ አባላት በገንዘብ እና በቁሳቁስ እያደረጉት ያለው እርዳታና ድጋፍ አበረታች ሲሆን ፣ በ "የኔታ ቤት" ስም በዛሬው እለት የተገኘው ይህ እርዳታ ቫይረሱን ለመከላከል በሚደረገው ርብርብ ከፍተኛ ድጋፍ እንደሚሆን ይታመናል።

በመሆኑም ለዳያስፖራው ማህበራሰብ ህጻናት የአገራቸውን ባህልና ወግ እንዲያውቁ እንዲሁም በኢትዮጵያ የቅድሜና እሁድ "ዮዮ" በተሰኘ የህጻናት የቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ ትምህርታዊ ቪዲዮዎች፣ ቀልዶች፣ የህጻናት ዜማዎች፣ ታሪኮችና ሙዚቃዎችን የሚያቀርበው እና በአቶ ዮሀንስ ዘርፉ የሚመራው "የኔታ ቤት" ስም አስተባባሪነት ለሀገራችን ለተበረከተው የ74,800 ማስኮች እርዳታ በኢትዮጵያ መንግስት ስም በብራስልስ የኢፌዲሪ ኤምባሲ ለለጋሹ ድርጅት እና ለአስተባሪዎቹ ከፍተኛ ምስጋናውን ያቀርባል።